# የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል
# CATERING AND TOURISM TRAINING CENTER

www.cttiedu.org Catering & TourismTraining Institute

ዜና መጽሔት

ቅጽ 2 ቁጥር 6




በህዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ





## የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሠልጠኛ ማዕከል አዳዲስ የተመደቡ የቦርድ አባላትና ነባሮቹ በማዕከሉ ጉብኝት አደረጉ፡፡

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ታህሳስ 26/2012 ዓ.ም

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሠልጠኛ ማዕከል አዳዲስ የቦርድ አባላት ተመደቡለት፡፡ የቦርድ አባላት ዘርፉን ሊደግፉ የሚችሉ የትምህርት ዝግጅት እና የካበተ ልምድ ያላቸው በመሆኑ ለተቋሙ ትልቅ አቅም እንደሚሆን ተገልጿል፡፡

የቦርድ አባላቱ ከተቋሙ ሃላፊዎች ጋር ባደረጉበት ወቅት ነባር የቦርድ አባል የሆኑት አቶ ቢንያም እንደተናገሩት በሚቀጥለው አምስት ዓመት በአዲስ አበባ ብቻ 20 ሺህ በሆቴል ሙያ የሠለጠነ ባለሙያ እንደሚ-ያስፈለግ ገልጸዋል፡፡

የቦርድ አባላቱ በሥልጠና ላይ ያሉ ሠልጣኞ-ችን ባነጋገሩበት ወቅት በተግባር ልምምድ ጊዜ በቂ ሥልጠና ለማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ እንዲመቻችላቸው ሰልጣኞች የጠየቁ ሲሆን በጥያቄያቸው መሠረት ከቦርድ አባላቱ ምላሽ እንደሚሰጣቸው ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ተናግረዋል፡፡

የቦርድ ሰብሳቢው ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሱ በበኩላቸው አዲሱ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርቶች ምላሽ የሚሰጥ በመሆኑ የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሠልጠኛ ተቋም በዘርፉ የሠለጠነ ባለሙያ በጥራትም በብዛትም ማቅረብ እንዲችል የሚመለከተን የቦርድ አባላት የድርሻችንን እንወጣለን ብለዋል፡፡ በተጨማሪም ባህላዊ የሆኑ ምግቦቻችን ወደ ሃገራችን የሚመጣ የውጭ ዜጋ እንዲሁም ኢትዮጵያዊው በሆቴል ቤት ከምግብ ዝርዝር እንዲያገኘው ይህ ተቋም የሥልጠናው አካል አድርጎ መያዝ እንዳለበት የቦርድ ሰብሳቢ ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሱ ተናግረዋል፡፡ በመጨረሻም ሠልጣኞች የሠሩትን ጣፋጭ ብስኩቶች ለእንግዶች ጋብዘዋል፡፡

## አዲስ የቱሪዝም ትምህርት ክፍል ሰልጣኞች በአዲስ አበባ የሚገኙ ሙዚዬሞችን ጎበኙ

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ
ታህሳስ 03/2012



በኢንስቲትዩቱ ቱሪዝም ትምህርት ክፍል የሚሰለጥኑ አዳዲስ ሰልጣኞች በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የቱሪስት መስህቦችን እና ብሔራዊ ሙዚየምን ጎበኙ፡፡ ጉብኝቱን የሚመሩት የቱሪዝም ትምህርት ክፍል መምህራን ለሰልጣኞቹ በከተማዋ የሚገኙ ባህላዊ፣ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ቅርሶችን አስጎብኝተዋል፡፡

አንዳንድ ሰልጣኞች ከጉብኙቱ በኋላ እንደገለጹት ጉብኝቱ ለቀጣይ ትምህርታቸው በጣም እንደሚጠቅምና ስለሃገራቸው ቀደም ያለ ታሪክ ለማወቅ እድል እንደፈጠረላቸው ተናግረዋል፡፡



## ለኢንስቲትዩቱ ሰልጣኞች የሙያ ስነምግባር ላይያተኮረ ስልጠና ተሰጠ፡፡

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ታህሳስ 27/ 2012 ዓ.ም

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት 800 ለሚሆኑ አዲስ ሰልጣኞች የሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪ ሙያ ሥነምግባር ላይ ያተኮረ ስልጠና ገነት ሆቴል ተሰጠ፡፡ ለሰልጣኞች መልዕክት ያስተላለፉት የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት የሙያ ሥነምግባር በተለይም ለሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪ ወሳኝ በመሆኑ ስልጣኞች ከስልጠና እስከ ስራገበታ ድረስ ሙያዊ ስነምግባርን በመላበስ በማገልገል የሀገራችንን ቱሪዝም ለማሳደግ መስራት አለባቸው ብለዋል፡፡

## የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማስልጠኛ ማዕከል የስልጠና ሂደቱ በተሻለ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ተገለጸ፡፡

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ታህሳስ 17/ 2012 ዓ.ም

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል የስልጠና ሁኔታን በሚመለከት የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎችና ሰራተኞች በተገኙበት ታህሳስ 16/2012 ዓ.ም በገነት ሆቴል ውይይት ተደርጓል፡፡ የአካዳሚክ ስራዎችን የመነሻ ጽሑፍ ያቀረቡት አቶ ግሩም ግርማ የተቋሙ የስልጠና ተደራሽነት ማደጉ፣ የሶፍትዌር ብልሽት መስተካከሉ፣ ሃምሳ ስምንት የስልጠና ሞጁሎች መዘጋጀታቸው፣ ቀርቶ የነበረው የዲግሪ መርሐ ግብር መጀመሩና የጥናትና ምርምር ስራዎች ከባለፈው የተሻለ ሁኔታ እየተከናወኑ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

## ዜና መጽሔት

አቶ ዳንኤል በቀለ የአስተዳደርና ልማት ዲን በበኩላቸው አዳዲስ አሰራሮችን በመዘርጋት ለስልጠናው የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በወቅቱ ግኙ መከናወኑን ገልጸዋል፡፡



በሌላ በኩል የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ለሃምሳ ዓመታት በዘርፉ ላይ ትኩረቱን በማድረግ የስልጠና፣ የማማከርና የጥናትና ምርምር ስራዎችን ሲያከናውን የቆየ ብቸኛ





የመንግስት ተቋም ሆኖ ሳለ የተቋሙን አቅም በማሳደግ በዲግሪና ከዚያ በላይ በሆነ የትምህርት ደረጃ ለማስተማር ተቋሙን ወደ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ለማሳደግ በተለያዩ ጊዜያት ለሚመለከተው አካል ቢቀርብም ሳይጸድቅ በመቆየቱ በስልጠና ሂደቱ ላይ ተጽኖ እየፈጠረ መሆኑ በውይይት መድረኩ ላይ ተገልጿል፡፡ ለሰልጣኞች የመኝታና የምገባ ስርዓቶች ባለመኖሩ የሚሰጣቸው 510 ብር የኪስ ገንዘብን ተጠቅመው ስልጠናቸውን ለመከታተል አስቸጋሪ መሆኑ ተብራርቷል፡፡

ለተነሱት ጥያቄዎች ማብራሪያ የሰጡት የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ደምቡ እንዲጸ-ድቅ ክትትል እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው ሁሉም የሚመለከተው አካል ርብርብ ማድረግ አለበት ብለዋል፡፡

የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬተር አቶ ገዛኸኝ አባተ በበኩላቸው በ2012 ትምህርት ዓመት የተሻለ የስልጠና ጥራት ለማምጣት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

### በሐረር፣በድሬዳዋና አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ ላይ ትምህርታዊ ጉዞ

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ታህሳስ 27/2012 ዓ.ም መነሻውን አዲስ አበባ ያደረገው የሰልጣኞች ትምህርታዊ ጉዞ መዳረሻውን ውቢቷ ሀረር ከተማ አድርጓል፡፡ የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ የሆኑት አቶ ሀብታሙ በላይ እንደገለጹት በከተማው አንድ የማህበረሰብ፣ አንድ የግልና ሁለት የመንግስት ሙዚዬሞች እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ ይህም ከተማዋን በኢትዮጵያ ከሚገኙ ከተሞች ከአዲስ አበባ ቀጥሎ በሙዚየሞች ቁጥር ሁለተኛ እንደ-ሚያደርጋት አቶ ሀብታሙ ተናግረዋል፡፡ እነዚህን ሙዜሞች ሰልጣኞች በሁለት ቡድን ተከፋፍለው በሰፊ ማብራሪያ ጎብኝተዋል፡፡



በመቀጠልም አመሻሽ ላይ የጅብ ምገባ ስርዓትም ተከናውኗል፡፡ በሶስተኛው ቀን የበረሐዋ ገነት የሆነችው ድሬዳዋ በመጓዝ የኢትዮጵያ ቀደምት ስልጣኔ የሆነውን ነባሩን የባቡር ጣቢያውንና በውሰጡ አሁን እየተሰሩ ያሉት ስራዎች ተጎብኝተዋል፡፡ በመቀጠልም ወደ አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ በማቅናት በፓርኩ ትምህርታዊ ጉብኝት አድርጓል፡፡ በጉዞ ላይ 75 ሰልጠኞች ተሳትፈዋል፡፡

## የሁለተኛ ዓመት የቱሪዝም ትምህርት ክፍል ሰልጣኞች በዝዋይ ከተማ ትምህርታዊ ጉዞ አደረጉ





ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ታህሳስ 06/2012 ዓ.ም በከተማው የሚገኙ ተፈጥሯዊ መስህቦችን ማለትም በኢትዮጵያ በስፋቱ ትልቁ የዝዋይ ሀይቅን በጀልባ ከአንድ ሰዓት ተኩል በላይ ተጉዞ በመሻገር በአካባቢው የሚኖሩ ደሴቶች ተጎብኝቷል፡፡ ከዝዋይ ሃይቅ ባሻገር አምስት ደሴቶች እንዳሉ አስጎቢኝው ተናግሯል፡፡ እነዚህም ገሊላ ፣ደብረ ሲና ፣ደብረ ጺዮን፣ ፋማት እና አይሱ ደሴት ተብለው እንደሚጠሩ፣ በውስጣቸው የተለያዩ ታቦታት እንዳሉም ተገልጿል፡፡

ከደሴቶቹ አንዱ ደግሞ አእዋፋት ብቻ እንደሚ-ገኙበትም ተገልጾልናል፡፡ ከደሴቶቹ በመመለስ ወደ ሁለት ሰዓት የሚደርስ ጉዞ ከኃይለኛ ንፋስ ጋር በሀይቁ ላይ በመጓዝ ወደ ዝዋይ ከተማ በመግባት የመጀመሪያው ጉብኝት ተጠናቋል፡፡

ሌላኛው የጉብኝት ስፍራ አብያታ ሻላ ሃይቆች ብሔራዊ ፓርክ ሲሆን በዚህ ፓርክ ውስጥ የተለያዩ አእዋፋትና የዱር እንስሳት ይገኙበታል፡፡ በተጨማሪም አብያታና ሻላ ሃይቆች ልዩነት ለሰልጣኞች ገለጻ ተደርጎላቸዋል፡፡ በመጨረሻም ወደ ላንጋኖ ሃይቅ በመጓዝ ዋና የሚችሉ ሰልጣኞቻችን ሲቦርቁበትና የማይችሉትን ሲያለማምዱ ተመልክተናል፡፡

የቱሪዝም ትምህርት ክፍል ኃላፊ አቶ ክዳኔ ገረሱ እንደገለጹት ይህ ጉብኝት የተግባር ትምህርት አካል በመሆኑ ሰልጣኞች ከትምህርታቸው ጋር በማዋሃድ ግብረመልስ እንደሚሰሩም ተናግረዋል፡፡

## የማሰልጠኛ ማዕከሉ የሰልጣኞች ደምብ ልብስ ተቀየረ፡፡

ሆ.ቱ.ማ.ማ ጥር 05/2012 ዓ.ም

የቀድሞ





አዲሱ

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ሰልጣኞች ደምብ ልብስ ነጭ ሸሚዝ፣ ጥቁር ከረቫት፣ሰደሪያና ሱሪ(ጉርድ ቀሚስ) የነበረው የተቋሙን ሎጎ መሰረት ወዳደረገው ጥቁር ሰማያዊ ሱሪ (ጉርድ ቀሚስ) ፣ የተቋሙ ሎጎ ያለበት፣ ጥቁር ሰማያዊ መስመር ያለው ነጭ ሸሚዝና ከረቫት ተቀይሯል፡፡

የሰልጣኞች የደምብ ልብስ እንዲቀየር ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ሰልጣኞች የደምብ ልብሱ እንዲቀየር ጥያቄ ማቅረባቸው፣ረዥም ጊዜ የቆየና አሁን ካለው የኢንዱስትሪው ፕሮቶኮል ጋር እንዲመጣጠን ለማድረግ ታስቦ መሆኑን የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ገልጸዋል፡፡ አዲሱን የደምብ ልብስ የሚለብሱት የአንደኛ አመት ሰልጣኞች ሲሆኑ የተቋሙን መለያ ሎጎ ለማስተዋወቅና ለሰልጣ-ኞችም በአዲስ የስልጠና መንፈስ ትምህርታቸውን እን-ዲከታተሉ እንደሚረዳቸው ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ሰልጣኞችም የደምብ ልብሱ በመቀየሩ ደስተኛ መሆናቸውን ገልጸው በተሻለ ሁኔታ ስልጠናቸውን ለመከታተል እንደሚረዳቸውም ገልጸዋል፡፡